ግንቦት 12/2000

## የሽብር ጠቀሜታው ለወያኔ አገዛዝ ብቻ ነው

በአዲስ አበባ ከተማ ውይይት በሚባል ከሚታወቁት አንድ የህዝብ መጓጓዣ ላይ በፈነዳው ቦምብ ንፁህ ዜጎች ህይወት መጥፋቱና በርካታዎችም መቁሰላቸው ተዘግቧል:: የወያኔ አገዛዝም በፍጥነት ለዚሁ ፍንዳታ ኤርትራን ከሷል:: ከዚህ ቀደምም መሰል ፍንዳታዎች ተካሂደው ንፁህ ዜጎች ላይ ጉዳት ደርሷል:: የዚህ ተራ ሽብር ተጠቃሚ ማነው ካልን ደግሞ ማን ቦምቡን አፈነዳው አላፈነዳው ዋናው ተጠቃሚ የወያኔ አገዛዝ ብቻ ነው:: ንፁህ ዜጎችን ማጥቃቱ መስመር አቅጣጫውን የሳተ ሽብር እንጂ በለውጥ ትግል ደረጃ የሚመዘገብ አይደለምናም ነው::

የለውጥ ታጋዮችና የሽብር አባወራዎች አንድ አይደሉም:: ሽብርተኞች ግራ ቀኙን ሁሉንም ገድለውና ሽብር ፈጥረው ውጤት የሚያመጡ ይመስላቸዋል:: በሚወስዱት እርምጃ ምንም ያላጠፋው ዜጋ ቢጠቃ አይሸበሩም:: ዋናው ዓላማቸው ማሸበር ነውና:: ይህ ደግሞ የሀገር ወዳድ ታጋዮች ምርጫ አይደለም:: ሀገር ወዳድ ታጋዮች ማጥቃት የሚፈልጉትና የሚያጠቁት ዋናውን ጠላት የወያኔ አገዛዝ ነው:: አስመሳይ ታጋዮች ወደዱም ጠሉም ለወያኔ አገዛዝ የሚጠቅሙት ደግሞ እርምጃቸው በመሰረቱ ሕዝብን አጥቅቶ ወያኔን ጠቃሚ በመሆኑ÷ አገዛዙ በድርጊታቸው ተጠቅሞና ተጠቂ መስሎ ግቡን ሊያሟላ ይጥራል:: በከተማ የውይይት (ሚኒባስ) መጓጓዣ የገዢው መደብ አባወራዎች አይንቀሳቀሱም:: ላምባ ወይ ነጭ ጋዝ ሊገዙ ቤንዚን ጣቢያ የሚሰለፉትም ባለሀብቶች አይደሉም:: በገዢው ክፍል ላይ ሽብርና ጭንቀትን ማስፈን ከተፈለገ በሚጎዳው መንገድ ማጥቃት እንጂ ሕዝብን ማሸበሩ ፋይዳ የለውም:: በጠመንጃ ኃይል ሥልጣን ይዞ ሕዝብ እያሰቃየ ያለው አስከፊ አገዛዝ የሚወስዳቸውን የሽብር ርምጃዎች÷ መቋቋም÷ መከላከልና ማጥቃት ሽብር ሳይሆን ተገቢና የሚደገፍ እርምጃ ነው:: ሰላማዊውን ሕዝብ ግን በፈንጂ መፍጀቱ በምንም መንገድ የሚደገፍ አይደለም::

በአዲስ አበባ የፈነዱት ቦምቦች ንፁህ ዜጎችን ሲገድሉ የወያኔ አገዛዝ በሁኔታው ለመጠቀም ጠላት ያላቸውን እየወነጀለ መቀጠሉ የታየ ነው:: በዚህ መንገድ የዜጎችን ንዴትና ቁጣ ቀስቅሶ ጠላቶቹ ላይ ድል ሊያገኝ ይፈልጋል:: በዚህ ደረጃ የወያኔ አገዛዝ ራሱ ቦምቦቹን አጠመደ÷ አፈነዳ የሚለው ክስ በቀላሉ የሚታለፍ አይሆንም:: በተቃራኒው ደግሞ በዚህ ዓይነት ተራ ሽብር በመሰማራት የመለስን አገዛዝ እናናጋለን በሚል ዜጎችን የሚገድሉ ካሉ በጊዜና በማያዋላዳ መንገድ ይህ ተራ ሽብር መሆኑና ተወደደም ተጠላም፤ ተፈለገም አልተፈለገም ለወያኔ አገዛዝ መጥቀሙ ሊነገራቸው ያስፈልጋል:: ኢሕአፓ ሕዝብን ሰለባ የሚያደርግ ማንኛውንም እርምጃና ሽብር የሚቃወም ነውና በሕዝብ ማጓጓዣ ውይይት ላይ ንፁህ ዜጋ በሚገኝበት ቦታ ፈንጂ የሚያጠምዱትን ሁሉ ያወግዛል፤ ይቃወማል:: አገዛዙን ማጥቃት ከተፈለገ በአገዛዙ ላይ ብቻ ማተኮር የግድ ነው:: መለስ ዜናዊና ጭፍሮቹ ውይይትን በመሰሉ የሕዝብ ማጓጓዣዎች አይሳፈሩም:: ለነጭ ጋዝ በቤንዚን ጣቢያ÷ በገበያ ለጠፉ ሸቀጦች በየሱቁ ሊገዙ አይሰለፉም:: "ተራ " ሆቴል አይገቡም፤ አይመገቡም:: ስለሆነም ዒላማን መምረጡ ወሳኝ ነው:: ይህ ሳይሆን ቀርቶ አላፊ አግዳሚውን መግደሉና ታገልን ማለቱ መቸም ቢሆን ሊደገፍ የሚችል አይደለም:: ማቹ ጭቁኑ ነውና እሰየው ማለቱ ከቶም የሚቻል አይደለም:: ለዚህም ነው ይህ ተራ ሽብር የወያኔ አገዛዝ አደረገው አላደረገው በመጨረሻ ደረጃ ጠቀሜታው ለወያኔ አገዛዝ የሚሆነው::

በመሆኑም ኢሕአፓ ይህን ዓይነቱን ሽብር ማን አደረገው ማን÷ በሚገባ ያወግዘዋል:: ለሕዝብ ቆመናል ወይም እየታገልን ነው የሚሉ ክፍሎች ጥቃታቸውን በወያኔ አገዛዝ ጭፍሮቹ ላይ ብቻ ማተኮር አለባቸው:: ይህ ሀገራዊ ግዴታ ነው:: የለም ብለው ሰልፋቸውን ከመለስ አገዛዝ

ጋር ያስተካከሉቱ ደግሞ ሳሩን እንጂ ገደሉን መች አየህ መባል ጊዜያቸው ነው::
ስለዚህም ዜጎች በወያኔ ጎዳና መጓዝ እንደሌለባቸው ኢሕአፓ ዳግም ያሳስባል:: እየተካሄደ ያለው ሽብር በሁሉም ጎኑ ጠቀሜታው ለወያኔ አገዛዝ ብቻ ነው ይላል ኢሕአፓ:: ለዚህም ነው ሽብሩ የወያኔ አገዛዝ ድርጊት ነው የሚለው ጥርጣሬና ክስ መሰረት ያለው የሚሆነው:: በሌላ በኩል ደግሞ በዚህ ዓይነቱ ድርጊት በመሰማራት ትግል ያካሄዱ የሚመስላቸው ካሉ ድርጊታቸው ተራ ሽብር ነውና ያቆሙት ዘንድ የምንመክራቸው::

ኢሕአፓ ሕዝባዊ ትግልን ይደግፋል::
ኢሕአፓ ሕዝብን የሚያጠቃ ሽብርን ይቃወማል::
ፀረ ሕዝብ ሽብርን በጋራ እናውግዝ::

EPRP
P.O.Box 73337
Washington DC, 20056
USA
Tel. 202-291-4217 Fax 202-291-7645

E-mail : ESPIC@aol.com

Website: www.EPRP.com

EPRP
BP 22
Bois colombes 92270
France